# የወባ በሽታ

የወባ በሽታ በዓይን በማይታይ የደም ጥገኛ ተህዋስያን በሆኑ ፕላዝሞዲየም በሚባሉ የፕሮቶዝዋ ዝርያዎች ምክንያት የሚመጣ በሽታ ሲሆን በዋናነት አኖፌለስ በምትባል ሴት ትንኝ ንክሻ አማካኝነት ከበሽተኛ ወደ ጤነኛ ሰው ይተላለፋል፡፡አንዳንድ ጊዜ ምልክቶቹ ከ48 እስከ 72 ሰዓት እየቆዩ በድጋሚ ይከሰታሉ፡፡ይህን የሚወስነው ግለሰቡን ያጠቁት ተሕዋስያን ዓይነትና በበሽታው ተይዞ የቆየበት ጊዜ ነው፡፡በሽታው በአብዛኛው የክረምት ወራት መውጣትን ተከትሎ ከመስከርም እስከ ታህሳስ በከፍተኛ ደረጃ የሚተላለፍ ሲሆን በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ ከበልግ ዝናብ በኂላ ከሚያዚያ እስከ ሰኔ በዝቅተኛ ደረጃ ይተላለፋል፡፡

የበሽታው ዋና ዋና ምልክቶች ትኩሳት፣ማላብ፣ብርድ ብርድ ማለት፣ራስ ምታት፣ማንቀጥቀጥ፣ማቅለሽለሽና፣ ማስታወክ፣ ድካም እና ቁርጥማት ዋናዋናዎቹ ናቸው፡፡በተመሳሳይ የወባ በሽታ በዋናነት የሚያሳዩት ምልክቶች ራስን መሳት፣ መመገብ ወይም መጠጣት አለመቻል በተከታታይ ማስታወክ፣ የሰውነት ፈሳሽ መሟጠጥ፣ ራስን ችሎ መቆምና መቀመጥ አለመቻል፣ ራስን ስቶ መውደቅ፣ የአይን ቢጫ መሆን፣ ከፍተኛ የደም ማነስ እና የአየር ቧንቧ ከረጢት እብጠት ናቸው፡፡

ለወባ በሽታ መጨመር ምክንያቶች የዓለም የአየር ንብረት ለውጥ፤ የክልሉ ሰማኒያ በመቶ የሚሆነው የመሬት ክፍል ለወባ መተላለፍ ምቹ መሆኑ፤ ከዚህ በፊት በፀረ ወባ ትንኝ ኬሚካል ርጭት ይሸፈኑ የነበሩ ወረዳዎች አለመረጨት፤ ህብረተሰቡ በወባ መከላከልና መቆጣጠር ተግባራት ላይ ንቁ ተሳትፎ አለማድረግ፤ የመኝታ አጎበር አጠቃቀም ባህል አናሳ መሆን እንዲሁም የአካባቢ ቁጥጥርና ተግባር አናሳ መሆን ናቸው፡፡ የወባ በሽታ ህመም ምልክት የታየበት ሰው ተገቢውንና ትክክለኛውን መድሃኒት እንዲያገኝና በወባ በሽታ መያዝ አለመያዙን ለማረጋገጥ በአካባቢው ወደ ሚገኝ ጤና ኬላ በመሄድ የደም ላቦራቶሪ ምርመራ በማድረግ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡

የወባ በሽታ መከላከያ መንገዶች የአካባቢ ቁጥጥር ስራ እንዲተገበር በማድረግ (ማፋሰስ፣ማዳፈን፣ ማጨድ) ማስጠቅጠቅ እንዲሁም በማይቻሉ ቦታዎች የፀረ እጭ ኬሚካል መጨመርና የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማጎልበትና ንቅናቄ መፍጠር፣የወባ በሽታ መከላከያ የመኝታ አጎበር በአግባቡ መጠቀም፣የቤት ውስጥ የፀረ ትንኝ ወባ ኬሚካል ርጭት ማካሄድ፤ትንኟ በሰውነት ላይ እንዳታርፍ የሚያደርጉ የተለያዩ ቅባቶችን መጠቀምና የወባ በሽታ ተጠርጣሪዎችን በ24 ሰዓት ውስጥ መመርመርና በሽታው የተገኘበትን ሰው ማከም፣የቤት መስኮቶችን ትንኝ ሊያስገቡ በማይችሉ ነገሮች መጋረድ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከሕብረተሰቡ የሚጠበቅበት ደግሞ የምኝታ አጎበርን ሁልጊዜና በአግባቡ መጠቀም፤አጎበሩ ሲቀደድ መስፋትና ሲቆሸሽ በቀላል ሳሙና በማጠብ ጥላ ስር አድርቆ መጠቀም፣በቤት ውስጥ ያለው አጎበር ለሁሉም ቤተሰብ የማይበቃ ከሆነ ቅድሚያ ለህጻናትና ለነፍሰጡር እናቶች እንዲጠቀሙ ማድረግ፣ በአካባቢው ያሉ ለወባ ትንኝ መራቢያ አመች የሆኑ ውሃ ያቆሩ ቦታዎችን በመለየት ማፋሰስ፣መጥረግ፣ የማዳፈን ስራዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ የወባ በሽታ ምልክት የታየባቸው ሰዎች በአፋጣኝ ወደ ጤና ተቋማት በመሄድ ምርመራና ህክምና ማድረግ፤በጤና ባለሙያ ትዕዛዝ መሰረት መድሃኒቶችን በአግባቡ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

ምንጭ፡- የአማራ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት (APHI)